# የተ.መ.ድ ፀጥታ ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ያሳለፋቸው የማዕቀብ ውሣኔዎች አተገባበር እንዲጠናከር ለማስቻል የተዘጋጀ እቅድ

## መግቢያ

ኤርትራ በቀጠናችን በምታራምደው ፀረ- ሠላም ፖሊሲና ለአሸባሪ ድርጅቶችና ሐይሎች በምትሰጣቸው ወታደራዊ፣ የማቴሪያልና ገንዘብ ድጋፎችና የተነሣ፣ የተባበሩት መንግሥታትና የፀጥታው ምክር ቤት እ.ኤ.አ በ2009 እና 2011 ሁለት የማዕቀብ ውሣኔዎችን /Sanctions Résolutions/ በተከታታይ ማሳለፉ ይታወሣል፡፡ የፀጥታው ምክር ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ዲሴምበር 2009 በኤርትራ ላይ ባስተላለፈው ውሣኔ - 1907 (2009) በዋናነት ሶስት ማዕቀቦችን የጣለ ሲሆን፣ እነሱም የጦር መሣሪያ፣ የጉዞ እገዳና የንብረት/ሀብት ማዕቀቦች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ኤርትራ ለአሸባሪ ሐይሎች የምትሰጣቸው ድጋፎችና የፀረ ሰላም እንቅስቃሴዋን አጠናክራ በመቀጣሏ፣ ምክር ቤቱ በ2011 አገሪቱ ከማዕድን ሽያጭ የምታገኘውን ገቢና ከዲያስፖራ አባላት የምትሰበስበውን 2% ታክስ ለአፍራሽ ተግባር እንዳታውለው እንዲሁም በአገሪቱ የሚደረጉ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችና የፋይናንስ ዝውውሮች ለፀረ-ሰላም እንቅስቃሴ እንዳይውሉ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር በአባል አገሮችና በአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት በኩል እንዲደረግ የሚጠይቅ ተጨማሪ የማዕቀብ ውሣኔ 2023/11 አሳልፏል፡፡

የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ የተጣለው ማዕቀብ ለመከታተል ያቋቋመው የሞኒተሪንግ ቡድን ሪፖርቱን በወር፣ በስድስት ወርና በአመት እያቀረበ የሚገኝ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ ቡድኑ በ2012 እና 2013 ባወጣቸው ሪፖርቶች በአንድ በኩል ኤርትራ በራሷና በሶማሊያ ላይ የተጣሉትን የጦር መሳሪያ ማዕቀቦች በመጣስ ለአልሸባብና በአካባቢያችን ለሚንቀሳቀሱ ፀረ-ሰላም ሐይሎች የወታደራዊ፣ የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፎችን እያደረገች እንደሆነ በማስረጃ በማስደገፍ ያረጋገጠ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አባል አገራት ውሳኔዎቹ በሚጠይቁት መሠረት የማዕቀቦቹን አፈፃፀምና የተከሰቱ ጥሰቶችን (Breaches) አስመልክቶ ወቅታቸውን የጠበቁ ሪፖርቶች ለተ.መ.ድ ዋና ፀሀፊና ለተቆጣጣሪ ቡድኑ እያቀረቡ እንዳልሆነና የማዕቀብ ውሳኔው በሚፈለገው ደረጃ ተፈፃሚ እንዳልሆነ አስታውቋል፡፡ በመሠረቱ የሞኒተሪንግ ቡድኑ ሪፖርት ማዕቀቦች ሳይነሱ እንዲቀጥሉ ለማድረግና የማዕቀብ ውሣኔዎቹን የሚጥሱ አካላትን ለማጋለጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው ይኸው በአባል አገራት በኩል ታማኝነት እንዲያገኝ ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በሌላ በኩል ከፀጥታው ምክር ቤት አባላት አንዳንዶቹ የማዕቀብ ውሣኔዎቹ ከመጽደቃቸው በፊት ያሳዩት ያለመደገፍ ፍላጐትና በመቀጠልም ተቆጣጣሪው ቡድን ያቀረባቸው የአፈጻጸም ሪፖርቶች ወገናዊነት ያጠቃቸዋል፣ ለአንድ ወገን ያደሉ ናቸው የሚል ስሞታ በማቅረብ፣ አንዳንድ አባል አገሮች ደግሞ የማዕቀቦቹን አፈፃፀም ከብሔራዊ ጥቅማቸው ጋር በማያያዝ፣ እንዲሁም ኤርትራ በማዕቀቦቹ ምክንያት

የገጠማት የውስጥና የውጭ ፈታኝ ሁኔታዎች (የኢኮኖሚ ችግር፣ ከዓለም አቀፍ ሀብረተሰብ መገለል ወዘተ…) እንዲሁም ትንሽ አገር መሆንዋ የተወሰኑ አገሮች sympathy እና understanding ማግኘቷ ለማዕቀብ ውሳኔዎቹ ተፈፃሚነት እንቅፋት እንደፈጠረ ይገመታል። ከዚህ በተጨማሪ የኤርትራ መንግሥት በተለያየ ጊዜያት፡-

- ማዕቀቡ በኢጋድ አባል አገራት ቀጥሎም በአፍሪካ ህብረት መሪዎች ጉባኤ ተቀባይነት አግኝቶ በተ.መ.ድ ፀጥታው ምክር መፅደቁን ወደ ጐን በመተው ጉዳዩ በአገራችንና በአንዳንድ ኃያላን መንግስታት ግፊትና ጫና የተጣለባት መሆኑና ይህው የኢትዮጵያና የሀያላን መንግሥታት ፍላጐት ለማሟላት የተደረገ መሆኑን እየገለፀች የምትገኝ መሆኗ፣
- ማዕቀቡ የአገሪቱን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጓተትና አገሪቱን ከድህነት ለመላቀቅ የምታደርገው ጥረት አደጋ ውስጥ መውደቁ ፣ በዚህ ምክንያት ህዝቡ ለረሀብና ለዕርዛት እንዲሁም የአገሪቱ ወጣት ሀይል ለአስከፊና አሰቃቂ የህገ ወጥ ዝውውር እንዲዳረግና ለከፍተኛ አደጋ እንዲጋለጥ አስተዋጾ እያደረገ እንደሆነ፣
- ማዕቀቡ ከአገሪቱ ጋር የሚዋሰኑ አገሮች ጋር ያለውን የድንበር አካባቢ ውጥረት እያስፋፋ እንደመጣና ይኸውም ለአገሪቱ አለመረጋጋትና በአጠቃላይ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ አደጋ ውስጥ የከተተው መሆኑ፣
- በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ በኩል ለሶማሊያም ሆነ ለሌሎች አማፅያን ብድኖች ምንም አይነት የወታደራዊ ፣ የማቴሪያል ወይም የፋይናንስ ድጋፍ የማትሰጥ መሆኑ እና
- የኤርትራ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት በውይይት ለመፍታት ፍላጐት ያለው መሆኑን

በመግለጽ የአንዳንድ አባል አገራትን አመኔታና ድጋፍ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ እንደምትገኝ ለመገንዘብ ተችሏል። ይህ ክቅርብ ጊዜ ወዲህ በኤርትራ መንግሥት እየተጠናከረ የመጣው የመለሳለስና ከአለም አቀፍ ሕብረተሰብ ጋር የጀመረቸው አዲስ engagement የማዕቀቦቹን ፀንቶ መቀጠልና አስፈላጊነት በድጋሚ እንዲጤን እያደረገው እንደመጣ ይገመታል።

የኤርትራው ፕሬዝዳንት በአንዳንድ አገሮች በቅርቡ ያደረጉት ጉብኝቶች፣ የፖለቲካ አማካሪያቸው በፓሪስ ከፀጥታው ምክር ቤት ማዕቀብ ኮሚቴ ሊቀመንበር ጋር ያደረገው ንግግር ወዘተ… ይህንኑ ዓላማ የያዙ እንቅስቃሴዎች እንደሆኑ መገመት አዳጋች አይሆንም። ኤርትራ ማዕቀቦቹን ከኤርትራ- ኢትዮጵያ የድንበር dispute ጋር ለማያያዝ፣ በተለይም አገራችን የአሜሪካን ድጋፍ በማግኘት የዓለም አቀፍ ሕግ በመጣስ ግዛቷን በሃይል እንደያዘች፣ ከድህነት ለመላቀቅ ለምታደርገው ጥረት ማዕቀቦቹ እንቅፋት እንደሆኑባትና በአጠቃላይ ተጠቂ (victim) መሆንዎን በተገኙ የአለም አቀፍ ሰብሰባዎችና መድረኮች መናገሯ የዚሁ እንቅስቃሴ አካል እንደሆነ መገመት አያዳግትም።

አገራችን በኤርትራ ላይ የማዕቀብ ውሣኔዎች እንዲተላለፉ የኢጋድ አባላት አገራትን በማስተባበር እንዲሁም በአፍሪካ ህብረትና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በግንባር ቀደምትነት መንቀሳቀስዋ የሚታወስ ሲሆን ውሳኔዎቹ ከተላለፉፍ በኋላ ግን የውሳኔዎቹን አፈፃፀም አስመልክቶ ጉዳዩን በባለቤትነት ስሜት ነክሶ በመያዝ በተቀናጀና ተከታታይትና ባለው መልኩ በዋናው መ/ቤትም ሆነ በውጭ አገር በሚኖሩ ኢምባሲዎቻችን ፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤትቻችንና ቆንስላ ጽ/ቤቶቻችን የተደረገው እንቅስቃሴ አነስተኛ ሆኖ ይታያል። ይህ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት የኤርትራ መንግሥት ማዕቀቦቹ እንዲነሱ እያደረገ ካለው አዲስ አቀራረብና ጥረት አኳያ በአገራችን በኩልም ማዕቀቦቹ እንዳይነሱ ጠንካራ እንቅስቃሴ ካልተደረገ በስተቀር ቀደም ሲል የማዕቀብ ውሣኔዎቹ እንዲተላለፉ የተደረገው ከፍተኛ ጥረት መና ሆኖ ይቀራል። ስለሆነም በኤርትራ በኩል የሚደረገው ጥረት ለመቀልበስ፣ ኤርትራ ማዕቀቦቹን እየጣሳች እንደምትገኝና የኤርትራን መንግስት እውነተኛ ባህሪውን በማስገንዘብ ማዕቀቦቹ በሚፈለገው ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑና እንዳይነሱ ለማድረግ በመስሪያ ቤታችን በኩል እቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል።

በዚህ መሠረት የተ.መ.ድ ፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ያሳለፏቸው የማዕቀብ ውሳኔዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በአጭር እና ረጅም ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት፣ አከናዋኝ አካላትና ተግባራቱ የሚከናወኑበትን የጊዜ ሰሌዳ የያዘ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

አባሪ፤

6 ገጽ ዕቅድ

## የተ.መ.ድ ፀጥታ ምክር ቤት በኤርትራ ላይ ያስተላለፋቸው የማዕቀብ ውሳኔዎች አተገባበር እንዲጠናከር፣ ለማስቻል የተዘጋጀ ዕቅድ

| ተ.ቁ | በአጭር ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት | አከናዋኝ | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | በኤርትራ ላይ የተጣሉት ማዕቀቦች ለምን መነሣት እንደሌለባቸው የሚያስረዳ ጽሁፍ (Aid Memoire) ማዘጋጀት፣ | የአለም አቀፍ ድርጅቶች ዳ/ጄኔራል | ተጠናቋል |
| 2 | ማዕቀቦቹ ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ለፀጥታው ምክር ቤት አባላት ለማሳሰብ እንዲቻል፣ መከተል የሚኖርብንን አካሄድ (approach) የሚያመላክት Concept Note ማዘጋጀት፣ | የአለም አቀፍ ድርጅቶች ዳ/ጄኔራል | ተጠናቋል |
| 3 | በኤርትራ ላይ የተጣሉት ማዕቀቦች ለምን መነሳት እንደሌለባቸው ከሶስተኛ ወገን ጋር ለሚደረግ ውይይት የሚያገለግል፣<br>- የመነጋገሪያ ነጥብ (Talking points) ማዘጋጀት፣<br>- የተ.መ.ድ ውሳኔዎችና ደጋፊ ዶክሜንቶችን (የሞኒተሪንግ | የአለም አቀፍ ድርጅቶች ዳ/ጄኔራል | ተጠናቋል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ቡድን ሪፖርት Excerpts ማዘጋጀት፣ የፀጥታው ምክር፣ የኢጋድና የአፍሪካ ህብረት ውሳኔዎችን ማጠናከር /Compile ማድረግ/፣ | | |
| 4 | ለፀጥታው ምክር ቤት አባላትና ለተ.መ.ድ ሴክሬታርያት አካላት /ለዋና ፀሀፊው፣ ለፖለቲካ ጉዳዮች ዲፓርትመንት ወዘተ../ ኤርትራ ማዕቀቦች እንዲነሳ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለች፣ የአገሪቱ አመራር ተጨባጭ የባህሪ ለውጥ እንዳለመጣና ማዕቀቦቹን መነሣት ሳይሆን ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ማስገንዘብ፣ | የኒውዮርክ ቋሚ መልክተኛ ጽ/ቤት | ከጥር 25 ቀን 2006 ጀምሮ |
| 5 | ኢምባሲዎቻችን፣ ቋሚ መልክተኛ ጽ/ቤቶቻችንና ቆንስላ ጽ/ቤቶቻችን በሚገኙባቸው አገሮቹ ያሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤቶች የሚመለከታቸው ከፍተኛ የስራ ሐላፊዎችን በአካል በማግኘት፣ ኤርትራ ማዕቀቡ እንዲነሱ እያደረገች ያለችውን እንቅስቃሴ ማጋለጥና በአገሃሩ ኤርትራ ማዕቀቦቹን እየጣሰች እንደምትገኝ የተቀጣጣሪ ቡድኑን ሪፖርቶች በመጥቀስ መነሳት ሳይሆን መጠናከር እንደሚገባቸው፣ አገሮቹም የውሳኔዎቹን አፈጻጸም በተመለከተ ለተ.መ.ድ ዋና ፀሐፊ ወቅታቸውን የጠበቁ ሪፖርቶች ማቅረብ እንደሚገባቸውና መረጃዎችንም ለተቆጣጣሪው ቡድኑ መስጠት | በውጭ አገሮች የሚገኙ ኢምባሲዎቻችን፣ ቋሚ መልክተኛ ጽ/ቤቶቻችንና ቆንስላ ፅ/ቤቶቻችን | ከየካቲት 1 ቀን 2006 ጀምሮ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | እንደሚጠበቅባቸው ማስታወስና ማስገንዘብ፣ | | |
| 6 | ኤርትራ ማዕቀቦቹ እንዲነሱ የምታደርገውን ጥረት በመግለፅ በአንፃሩ ግን ማዕቀቦቹን እየጣሰች ለመገኘቷ የተቀጣጣሪ ቡድኑ ተከታታይ ሪፖርቶች እንደሚያረጋግጡ በማስረዳት ማዕቀቦቹ እንዳይነሱ በአዲስ አበባ ለሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ፣ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች፣ የአውሮፓ አገሮች ፣ የኤዥያና ኦሽንያ አገሮችና የሰሜንና የደቡብ አሜሪካ አገሮች አምባሳደሮች፣ የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር፣ የሰላምና ፀጥታ ካውንስል አባላትና ለሰላምና ፀጥታ ኮምሽነር እንዲሁም አግባብነት ያላቸው የተ.መ.ድርጅቶችና ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በመለየትና ቅደም ተከተል በማውጣት በአንክሮ ማስገንዘብ፣ | የበላይ አመራር፣ የአፍሪካ ሕብረት ቋ/መ/ጽ/ቤት- የአለም አቀፍ ድርጅቶችና አህጉራዊ ዘርፍ ዳ/ጀኔራልዎች | ከየካቲት 1ቀን 2006 ጀምር |
| 7 | የኤርትራ መንግሥት በውጭ አገር ከሚገኙ ኤርትራውያንና ትውልደ ኤርትራውያን የሚሰበስበውን የDiaspora Tax ለፀረ-ሰላም ተግባር እንዳይውል፣ በተለይ ተቆጣጣሪ ቡድኑ | አገሮች የሚገኙበት ኢምባሲዎችና ቋሚ | ከየካቲት 10 ቀን 2006 ጀምር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ባቀረበው የአገሮች list የተጠቀሱት አገሮች[1] ውስጥ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ የሚያስችል የሕግ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ መጠየቅ፣ | መልዕክተኛ ጽ/ቤቶች | |
| 8 | በፀረ-ሰላም ተግባራት በቀጥታ ተሳታፊ የሆኑ የኤርትራ የፖለቲካና ወታደራዊ አመራር አባላት በኮሚቴው Listing ውስጥ እንዲካተቱ የተደረገው ጥረት ምን ላይ እንደሚገኝ በማወቅ በቀጣይ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ሐሳብ ማቅረብ፣ | የኒውዩርክ ቋሚ መልክተኛ ፅ/ቤት | ከየካቲት 10 ቀን 2006 ጀምሮ |
| 9 | ኤርትራ ከማዕድን ሽያጭ የምታገኘው ገንዘብ ለፀረ-ሠላም ተግባር እንዳይውል መቆጣጠሪያ እንዲሆን የታሰበው Due diligence guidelines ዝግጅት በመጓተቱ የምክር ቤቱን አባላት፣ የSanctions Committee ሊቀመንበር እና የMonitoring Group አባላትን በማነጋገር ሂደቱን ማፋጠን፣ | የኒውዩርክ ቋሚ መልክተኛ ፅ/ቤት | ከየካቲት 15 ቀን 2006 ጀምር |

---

[1] አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ ዴንማርክ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ እስራኤል ጣሊያን፣ ኬንያ፣ ኖርዌይ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ደቡብ ሱዳን ፣ ሱዳን፣ ስዊድን፣ ስዊዘርላንድ፣ ኡጋንዳ፣ የተባበሩት አረብ ኢሚሬትስ፣ እንግሊዝና አሜሪካ

| | በረጅም ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት | አከናዋኝ | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 10 | የMonitoring Group አባላትን በማግኘት የማዕቀቡ ውሣኔዎች አፈፃፀምን አስመልክቶ ቀጣይነት ባለው መልኩ መረጃ መለዋወጥና በሚያቀርባቸው ሪፖርቶች ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ መጣርና ከአባላቱ ጋር ተቀራርቦ መስራት፣ | የኒውዮርክ ቋሚ መልክተኛ ፅ/ቤት | ከየካቲት 20ቀን 2006 ጀምሮ |
| 11 | ሞኒተሪንግ ቡድኑ በማዕቀብ ኮሚቴ በኩል ለምክር ቤቱ የሚያቀርባቸው ሪፖርቶች ውስጥ የሚካተቱና የማዕቀቦችን አፈፃፀም የሚያጠነክሩ recommendations በምክር ቤቱ ተቀባይነት እንዲያገኙ፣ /welocme/ የምክር ቤት አባላቱን የማግባባት ሥራ መሥራት፣ | ኒውርክ ቋሚ መልዕክተኛ ፅ/ቤት | ከየካቲት 30 ቀን 2006 ጀምሮ |
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12 | በሞኒተሪንግ ቡድኑም ሆነ በዋና ፀሀፊው የሚቀርቡ የአፈፃፀም ሪፖርቶች advance copy አግኝቶ መላኩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሪፖርቶቹ ከመውጣታቸው በፊት ከሚመለከታቸው የተ.መ.ድ ጽ/ቤት (secretairat departments) ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ቢቻል በምንፈልገው መንገድ ካልሆነም የማይጐዱን ሪፖርቶች እንዳይወጡ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ | የኒውርክ ቋሚ መልዕክተኛ ፅ/ቤት | ከየካቲት 1 ቀን 2006 ጀምሮ |
| 13 | ማዕቀቦቹ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተለይም በኤርትራ በኩል ማዕቀቦቹ እንዲነሱ የሚያደርገው ጥረት እንዳይሳካና የማዕቀቦቹም አፈፃፀም እንዲጠናከር ለማስቻል ወደ ኒውዩርክና ሌሎች የሚመረጡ አገሮች የሥራ ጉብኝት ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ | አለም አቀፍ ድርጅቶች ዳ/ጄኔራል፣ ኒውዩርክ ሚሲዮንና ጉብኝቶች የሚደረግባቸው ኢምባሲዎች | __________2006 ጀምሮ |
| 14 | በኤርትራ ላይ የተጣሉ ማዕቀቦች ተፈፃሚ ለማድረግ በቋሚነት ክትትል የሚያደርግ፣ የሚያስተባብርና አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ እንዲቻል መ/ቤታችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው መ/ቤቶችና አካላት የሚገኙበት ኮሚቴ የሚቋቋምበት ሁኔታ መከታተል፣ | አለም አቀፍ ድርጅቶች ዳ/ጄኔራል | ከየካቲት 15/2006 ጀምሮ |